# General Relief Society Meeting
# Saturday, September 24, 2011

አትርሳኝ

በፕሬዘደንት ዲየትር ኤፍ. ኡክዶርፍ
የቀዳሚ አመራር ሁለተኛ አማካሪ

ውድ እህቶች ዛሬ ከናንቴ ጋር በመሆነ ምንኛ ደስታ ነው። እኔ ሁል ጊዜ ለዚህ አመታዊ አጠቃላይ የሴቶች መረዳጃ መህበር ስብሰባ ለምሰጠው መልክት ወደፍት እመለከታለሁ። ለቤተክርትያን እህቶች ትንሽ ቃል በማለቴ ክብር ይሰማኛል።

በቅርቡ ከባለቤቴና ሴት ልጄ ቆንጆ ጓሮ ውስጥ ተጉዘን ነበር። በእግዚአብሄር ቆንጆ ፍጥረታት ተደነኩኝ። ከዝያም ከአስደናቅ እንቡጦች ትንሿን አበባ አስተወስኩኝ። የዝህን አበባ ስም አውቃለሁ ምክንያቱም ከልጅነቴ ጀምሮ ጣፋጭግንኙነት ነበረኝ። አበባውም ዝርያ ይባላል።

ይህ ትንሽ አበባ ለአመታት ትልቅ ነገር የሆነበት ምክንያት አላውቅም። ምናልባትም ከትላልቅ አበባዎች ትንች በመሆኑ አይን ባይስብም ግን ደማቅ ነው። አበባው በደማቅ ቀለም ከሰማያዊ ደማና ጋር እንደ መስታወት ያንፀባርቃል። አንዱ ምክንያት የምወደው ለዝሁም ነው።

የአበባው ስም በብዙ ቋንቋ ልመና ይባላል።፡ በጀርመን አፈታሪክ እግዛብሄር ለሁሉም አበባዎች ስም ከሰጠበኃላ ለአንዱ ስም ሳይሰጥ ቀረ የሚል ነበር። ትንሹ ድምፅ እግዚአብሄር ሆይ አትርሳኝ ብሎ ተናገረ። እግዛብሄርም በመመለስ ይህ ስሙነው አለ።

ዛሬ ምሽት ይህችን ትንሽ አበባ እንደ ምሳሌ እጠቀማለሁ። አምስቱ የአበባ ቀንበር በፍፁም የማንረሳው አምስት ነገርን አሳሰበኝ።

መጀመሪያ፣ በእራሳችሁ ትዕግስተኛ መሆንን አትርሱ።

አንድ ነገር እንድትረዱልነግራችሁ ምኞቴ ነው። እናንተና እኔ ፍፁም እንዳልሆን እግዚአብሄር ያውቃል።

እናንተ ፍፁም ናቸው ብላችሁ የምታስቡት ሰዎች እንድልሆኑ እግዛብሄር ያውቃል።

የራሳችን ድክመት ከሌሎች ጋር ለማወዳደር ብዙ ጊዜ ይፈጅብናል። ይህም ማሳካት የማንደርስበት ደረጃ ላይ ይጥለናል። በዝሁም ውጤት ጥሩ ጥረታችን አናከብርም፣ ምክንያቱም ሌሎች ከሚያድርጉት ያነሰ በመሆኑ ነው።

ሁሉም ሰዎች ብርታትና ድክመት አላቸው።

ብርታት መኖራችሁ ጥሩ ነው።

ድክመት መኖራችሁም ምድራዊ ልምድ ነው።

እግዛብሄር ድክመታችን ሁሉ ወደ ብርታት እንድንለውጥ ይረዳናል።[1] ይህ የጅምጊዜ ዕቅድ እነሆነ እሱም ያውቃል። እንደ እሱ[2] ፍፁም እንድንሆን ይፈልጋል። በደቀመዛመርት መንገድ የሚንጓዝ ከሆነ አንድ ቀን ይሳካል። አሁን ፍፁም ስላልሆናችሁ ምንም አይደለም። ሥራችሁን ቀጥሉ እንጅ እራሳችሁን ቅጣት ላይ አታድርሱ።

ውድ እህቶች ብዙዎቻችሁ ስለሌሎች ድክመት ወሰን የሌለው ርህራሄና ታጋሽነት አላችሁ። በራሳችሁም ታጋሽነት እና ርህራሄ እንድኖራችሁ አስታውሱ።

ለጊዜውም ስለቤታችሁ፣ ቤተሰባችሁ ግንኙነት፣ ስለ ትምህርትና እና ሥራችሁ፣ እና ስለ ቤተክርትያን ተሳትፎያችሁ መሳካት ምስጋና አቅርቡ። እንደ ትንሹ አበባ ይህ ስከታመነት ለናንቴ ትንሽ ለመስል ይችል ይሆናል ወይምበሌሎች ዘንድ ላይታወቁ ይህናል፣ ግን ለእግዝአብሄር ትንሽ ስላልሆነ ያስታውሳል። መሳካት ፍፁም መሆን አለበት ብላችሁ የምታስቡ ከሆነ የህይወት ጣፋጭልምዶችን ታጣላችሁ።

ለምሳሌ የቤተሰብ የቤት ምሽት በየሳምንቱ እንደ ፍቶ ፍፁም መሆን አለበት ማለት ሌሎችን ልያሰቃይ ስለምችል ጥሩ ምርጫአይደለም። ይህን ከማድረግ ከቤተሰብ ጋር ምን የሚያስደስት እና መንፈሳዊ ሆኖ አንድ ላይ ልያመጣን ይችላል? ብላችሁ እራሳችሁን ጠይቁ ። የዝህ አይነት የቤተሰብ የቤት ምሽት አዎንታዊ ዘለቀታ ልኖረውይችላል።

ወደ ፍፁማዊነት ጉዞያችን ረጅምነው፣ ግን በትንሹ ጉዞ እንኳ ደስታ ማግኘት እንችላለን።

ሁለተኛ በደግን ሞኝነት መስዋዕት መሀከል ያለው ግንኙነት፣

ተቀባይነት ያለው መስዋዕትነት አንድን ጥሩ ነገር ለተሻለ ዋጋ አሳልፈን ስንሰጥ ነው።

በህልም የተቸገሩትን ልጆች ለመርዳት ትንሽ እንቅልፍ ማጣት ጥሩ መስዋዕትነት አለው። ለሴት ልጅ የሰንበት ቀሚስ ተብሎ ጠንነታችንን አስጊ ሁነታ ላይ መታል ጥሩ መስዋዕት አይደለም።

መፅሀፍ ቅዱስን በትጋት በማጥናት ማስተማር ጥሩ መስዋትነት ነው። ለያንዳንዱ የክፍል አባል የቤት ማሰሮ አሰራር ለማስተማር ብዙ ጊዜ መፍጀት ጥሩ መስዋዕትነት አይኖረውም።

የያንዳንዱ ሰው ሁነታ ልዩነት አለው፣ ለአንዱ መስዋዕት ማድረግ ሌለላው ቅል ልሆን ይችላል።

የራሳችን ሁነታ ልዩነት እንደት መለየት እንችላለን? የበለጠ አስፈላጊ ለሆኑት ነገሮች ትኩረት ማድረጋችን እራሳችን መጠየቅ እንችላለን። ብዙ ደግ የሆነ ነገር መስራት ይቻላል፣ ግን ሁሉን ነገር በአንዴ መስራት አይቻልም። ለዘለቀታ ነገር ጥሩ መስዋዕት ስናደርግ የሰማይ አባታችን የበለጠ ደስ ይለዋል። ይህም አንዳንደ ትንሽ መኮትኮትን ይጠይቃል። ከትልቅ የጓሮ አበባዎች ትንሹን አበባ መንከባከብ ይሆናል።

ሶስተኛ በአከባብያችሁን ያለውን ደስታ አትርሱ፣

ተወዳጅነት ባለው የልጆች ታሪክ ቻርል እና የቾኮላት ፋብሪካ ዊል ዋንካ የከሬሜላ ሰሪው በተጠቀለሉት አምስት ከሬሜላ ወርቃማትኬት በመደበቅ ይህን ያገኘ ፋብሪካየን ለመጎብኘት አሸናፍ በመሆን ለዕድሜልክ ቸኮላቴን ያገኛል ብሎ ተናገረ።

በያንዳንዱ ወርቃማትኬት ይህ ነው የተፃፈው፤ ይህን ወርቃማትኬት ለመፈለግ ዕድለኛ ለሆናችሁ። በሱቅ ውስጥ ለናንተ ቆንጆ ዕቃ አለ። ብዙ የሚያስደንቁ ነገሮች ይጠብቃችዋል። ይህ የሚያስደንቅ ነገር ከሚታስቡት

በላይ ያስገርማችዋል። በህላችሁ እንኳ ይህ እንደምደርባችሁ አታስቡም። ቆይ ታያላችሁ።[3]

በታሪኩ የአለም ህዝቦች ወርቃማውን ትኬት ለመፈለግ ፍላጎት ነበራቸው። አንዳንዶቹ የወደፍት ደስታቸው በዚሁ ወርቃማ ትኬት በእጃቸው መውደቅ ላይ እንደሆነ ተሰማቸው። በዝሁም የተነሳ በኬሬሜላ የሚመጣውን ቀላል ደስታን መርሳት ጀመሩ። ከሬሜላው ወርቃማ ትኬትን ያቀፈ ካለሆነ ተስፋ አስቆራጭ ሆነ።

ዛሬ ብዙ ሰዎች የራሳቸውም ወርቃማ ትኬትን ይጠብቃሉ፣ ትኬቱም ሁል ጊዜ የተመኙትን የደስታ ቁልፍ እንደያዘ ያምናሉ። ለአንዳንዶች ወርቃማው ትኬት ጋብቻ፣ ሌለሎች ጥሩ ቤት፣ ሌለሎች ከሀሳብ ነፃ መሆን ነው።

ስለ ፃድቅ ምኞት ምንም አይደለም፣ "ደግና ጥሩ የሆነውን እንመኛለን።"[4] ችግር የሚመጣው ወደፍት ለምፈጠረው ነገር ደስታችን ወደ ኃላ ስንይዝ ነው።

አንድት ሴት ከማንኛውም በላይ የክህነት ሥልጣን የያዘውን ባል በቤተመቅደስ ማግባት ትፈልጋለች። ይህን ዕድሜዋ ሙሉ ተመኘች። ምንኛ ቆንጆ እናትና አፍቃሪ ሚስት ትሆናለች። ቤቷ በፍቅር የተሞላ ይሆናል። መራራ ቃል በፍፁም አይወጣቸውም። ምግብም አይቃጠለም። ለጆቻቸው ከጓደኛ ጋር ጊዜ ከማሳለፍ ከአባትና እናታቸው ጋር ያመሻሉ።

ይህ ውእቃማ ትኬቷ ነው። ኑሮዋን ሁሉ በዝህ ላይ ትኩረት አድርጋለች። ከአለማት ሁሉ ይህን ተመኘች።

ግን በፍፁም አልሆነም። ከጊዜ በኃላም መራራና ተናዳጅ ሆነች። እግዛብሄር ፃድቅ የሆነ ፍላጎቷን ለምን እንዳልሰጣት አልተረዳችም።

አንደኛ ደረጃ ት/ቤት አስተማር ነበረች። ሁል ጊዜ ከልጆች ጋር ስለሆነች ወርቃመ ትኬቷ አለመምጣቱን ያስታውሳታል። ከጊዜም በኃላ ተስፋ ቆረጠች። ሰዎችም ከሷ ጋር መሆን አልፈለጉም። ተስፋ የመቁረጥ ሁነታዋን ወደ ትምህርት ቤት ልጆች ወሰደች። የቁጣስሜቷን መቆጣጠር አልቻለችም።

ይዚህ ወድሴት ታሪክ ስለ ወርቃማትኬቷ ተስፋ መቁረጥ ያላትን በረከቶች እንዳታስታውል አደረጋት። ቤበቷ ልጆች አልነበራትም ግን በክፍል ውስጥ በልጆች ተከባለች። በበተሰብ አልተባረከችም ግን ጌታ እንደ አስተማሪነት በመቶ የሚቆጠሩትን ለደግ እንድታነሳሳ ዕድል ሰጥቷል።

የዚህ ዋና ትምህርት ቀናችንን አበባን ለመጠበቅ ካሳለፍን በአከባቢያችን ያሉትን ቆንጆ ነገሮች እናጣለን።

ይህም ምኞት አይኑረን ማለት አይደለም። የተሻለ ነገር ለመፈፀም ማቋረጥ የለባችሁም። ፃድቅ ለሆነ የልባችሁን ምኞት አቷቋርጡ። ግን ደህና ኑሮ ለሚያኖር ቀላል የሆነ ነገር ዓይናችሁን እና ልባችሁን አትዝጉ።

የማቃቸውደስተኛ ሰዎች ወርቃማትኬት የሚፈልጉ አይደሉም፣ ዋጋ ላለው ነገር ምኞት ያላቸውእና በዕለቱ ሁነታ የሚደሰቱ ናቸው። እነሱ ናቸው ደርጃ በደረጃ በህይወታቸው የምስጋና ስሜትን የሚፈጥሩ።

አራተኛ የወንጌልን “ለምን” አትርሱ።

አንዳንዴ በኑሮያችን ሳይታወቅ የኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌልን እንደ ትንሿ አበባ ዋና ገፅታን ችላ እናደርጋለን። እንደ ቤተክርስትያን አባልነታችን ሥራችን ማሟላት ስገባን አንዳንዴ ወንጌል ካለን ሁነታዎች ተጨማሪ የሥራ ዝርዝር እንደሆነ እናያለን። ጌታ ምን መስራት እንዳለብን እና እንዴት መድረግ ላይ ትኩረት ማድረግ አለብን። ግን አንዳንዴ ለምን እንደሆነ እንረሳለን።

ውድ እህቶች የኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል ግዴታ አይደለም፣ በአፍቃር አባታችን በዝህ ህይወት ወደ ሰላምና ደስታ የሚመራና በምመጣው ህይወት ክብር ላይ የሚያደርስ መንገድ ነው። የህያውነትን ወንጌል የሚሰነጥቅ ብርሀን ነው።

ወንጌልና የሥራውን አስፈላጊነት በመረዳት፣ ....የሰማይ አባታችን ለመኖር ይህን ዛዴ ለምን እንደሰጠን መረዳት፣ እና ይህ የህይወታችን

መሰረታዊ መሆኑን ስንረዳ ወንጌል ሸክምከመሆን ደስታነ አስደሳች ይሆናል። ጣፋጭዕንቁ ይሆናል።

የደቀመዛመርት መንገድ ስንጓዝ አይናችን ወደ መሬት በማየት የሥራ ግዴታውን ብቻ ማስብ የለብንም። የምድር ቆንጆነት እና መንፈሳዊ አቀማመጡን ሳንረዳ መጓዝ የለብንም።

ውድ እህቶች ለግርማዊ፣ ለቆንጆነት፣ ደስታፍላጎት የኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል ለምን መፈለግ እንዳለባችሁ አስታውሉ።

ታዛዥመሆን ትክክለኛ መንገድ ላይ ያደርገናል። የታዛዥነት ምክንያት ድርጊታችን በማንፃት ተራውን ወደ ግርማዊነት ይለውጣል። የትንሽ ድርጊት ታዛዥነትን ቅዱስን ድርጊት ያጎላ ያደርጋል።

ጌታ እንድምወዳችሁ አስታውሱ፣

በልጅነቴ ያችን ትንሽ አበባ ስመለከት አንዳንዴ አስፈላጊ እንዳልሆንኩ የትንሽነት ስሜት ይሰማኝ ነበር። በቤተሰቤ ወይም በሰማይ አባት ልረሳ እንድምችል አስብ ነበር። በአንድ ሰው እንደምታወስ በጣም እፈልግ ነበር።

ከአመታት በኃላ የወጣቱ ልጅ ርህራሄ ልመለከት ችያለሁ። እንዳልተረሳሁ አሁን አውቃለሁ።

አሁን ሌላ ነገር ነኝ። እንደ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ሀዋሪያነቴ በልቤ እምነት እርግጠኛነት እናንተም እንዳልተረሳችሁ እመስክራለሁ።

አልተረሳችሁም።

ምንምእንኳ ቀናችን ችግር ያለበት ብመስልም፣ አስፈላጊ እንዳልሆናችሁ ብሰማችሁም፣ ጭንቀት ብሰማችሁም የሰማይ አባታችሁ አልረሳችሁም። ወሰን በለለውይወዳችዋል።

በዩንቨርስ ሀያልግርማዊነት ባለው እንደምትታወሱ አስቡ። ወሰን በሌለው ቦታና ጊዜ ንጉስ የሚትወደዱ ናችሁ።

ኮከብን የፈጠረ እሱ በስማችሁ ያውቃችዋል። እናንቴ የመንግስቴያቱ ሴት ልጆች ናችሁ። ደራስው እንደፃፈው፡

“የጣቶችህን ሥራ ሰማዮችን ባየሁ ጊዜ፥ ጨረቃንና ከዋክብትን አንተ የሠራሃቸውን፥

“ታስበው ዘንድ ሰው ምንድር ነው? ትጎበኘውም ዘንድ የሰው ልጅ ምንድር ነው?

“ከመላእክት እጅግ ጥቂት አሳነስኸው፤ በክብርና በምስጋና ዘውድ ከለልኸው። ”[5]

የሱስ ልጆች ስለሆናችሁ እግዛብሄር ይወዳችዋል። ስህተት ብትፈፅሙም የወዳችዋል። ብቸኛነት ብሰማችሁ ወይም ፍፁም ባትሆኑም ይወዳችዋል።

የእግዚአብሔር ፍቅር የሚያድን ነው። የሱን መለኮታዊ ፍቅር ለህይወታችሁ ከጋበዛችሁ ማንኛውንም ቁስል ይሸፍናል፤ የቆሰለ ልብም ያድናል፤ ሀዘንም ለስላሳ ያደርጋል።

ወድ የሴቶች መረዳጃ መህበር እህቶች ከሚታሰቡት በላይ ወደ ሰማያት ቀርባችዋል። ከሚታስቡት በላይ እየተጓዛችሁ ነው። እምነትን እና የግል ፃድቃንነትን እየጨምራችሁ ህዱ። ዳግመኛ የተመሰረተውን የኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል በህይወታችሁ ተቀበሉ። በቤተክርስትያን የእንቅስቃሴ ስጦታን ተደሰቱ። በተባረከው የሴቶች መረዳጃ ማህበር አገልግሎት ስጦታን

ተደሰቱ። ቤተሰቦችን አጠናክሩ። የጌታን እና የናንቴን እርዳታ የሚያስፈልጋቸውን ፈልጉ።

እህቶች ስለዛች ትንሽ አበባ የሚያነሳሳ እና ልብ የሚማርክ ነገር አለ። ኑሮያችሁን ጣፋጭየሚያደርግ ምሳሌ እንድሚሆን ምኞቴ ነው። በራሳችሁ ላይ ታጋሽና ርህራሄ እንድኖራችሁ አትርሱ፣ አንዳንድ መስዋዕቶች ከሌሎች የተለዩ ወርቃማን ትኬታችሁን አትጠብቁ። የኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል መንፈሳዊነት እንደምሰጣችሁ አትርሱ። የተባረከው የሰማይ አባታችሁ ያውቃችዋል ፣ ይወዳችዋልም።

ለማንነታችሁ አመስግናለሁ። ለብዙሀን ላደርጋችሁ ወስን የሌለው ፍቅራችሁ እና አገልግሎት አመሰግናለው። ለቤተሰብ ፣ ለቤተክርስትያን ፣ እና ለአለም ህዝብ ላመጣችሁ የወንጌል ደስታ አመሰግናለሁ።

እንወዳችዋለን። በእግዚአብሄር መንግስት በእውነት ዕንቁ ሴቶች መሆናችሁን ፀሎቴና በረከተ ነው። በተቀደሰው ስሙ ኢየሱስ ክርስቶስ አሜን።